# ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 30 ኛ ሳምንት

## ልደታ ለማርያም

### ዓላማ

- እግዚአብሔር ዘወትር በጸሎትና በታማኝነት የሚጠብቁትን ምኞታቸውን ይፈጽማል፡፡
- በዛሬው ትምህርታችንም በትዕግሥት፣ በታማኝነት እና በጸሎት ጸንተው ውድና ልዩ ልጅ ስለተሠጠቻቸው ኢያቄም እና ሐና እንማራለን፡፡
- እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የሚሆን ልዩ ስጦታ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችውን ድንግል ማርያምን እንዴት እንደሠጣቸውም እናያለን፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1.ጌታችን ደቀመዛሙርቱን በባሕር ዳርቻ ሲያያቸው ምን ይሠሩ ነበር?

2.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

3.ቅ.ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን ሲያውቅ ምን አደረገ?

### ትምህርቱ

- የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ድንግል ማርያም ግንቦት 1 ቀን ተወለደች፡፡
- አባትዋ ኢያቄም እናትዋም ሐና ይባላሉ፡፡ሐና እና እያቄም በጋብቻ ለረጅም ጊዜ ሲኖሩ ልጅ አልነበራቸውም፡፡
- ሰዎችም ልጅ ያልሠጣቸው በኃጢያታቸው እንደሆነ ይነግሩዋቸው ነበር፡፡ ኢያቄም እና ሐና ግን በጣም ታማኞች እና ዘወትርም ልጅ እንዲሰጣቸው ወደ እግዚአብሔር ተስፋ ባለ መቁረጥ የሚጸልዩ ትጉህ ጥንዶች ነበሩ፡፡
- አንድ ቀን የእግዚአብሔር መልአክ ለኢያቄም ተገልጾ ልጅ እንደሚሠጣቸው አበሠረው ኢያቄም ለሐና ነገራት ሐናም በእምነት ተቀብላ እና አምና ትኖር ነበር፡፡
- ሁለቱም በሕልም ተረድተውም ሐና ጸነሠች፡፡የመውለጃ ጊዜዋ አልፎ ስለጸነሠችም ዘመዶችዋ ተደነቁ፡፡
- ሐና አንድ ዓይና አክስት ነበረቻት፡፡አንድ ቀን ሐና መጸነስዋን ስምታ ሆድዋን በእጅዋ ደስሳ ካረጋገጠች በኋላ ዓይኗን በዚያው እጅዋ ስትነካው ዓይንዋ በራላት፡፡
- ሌሎች ሰዎች ይሄን ተዓምር ሰምተው በመምጣት በተዓምር ተፈወሱ፡፡ነገር ግን አይሁድ ቀንተው ሐና እና ኢያቄም እንዲሠደዱ አደረጉ፡፡ወደ ሊባኖስ ተራራ ተሠደዱ በዚያም ግንቦት 1 ቀን ሐና ቆንጆዋንና ተወዳጅዋን ልጅ ወለደች ስምዋንም ማርያም አለቻት፡፡
- እናደስለታቸውም ድንግል ማርያም እስከ 15 ዓመትዋ በቤተመቅደስ እያገለገለች ኖረች፡፡
- እግዚአብሔርም በቅድስና ኖረው በንጽህና ከወለድዋት ልጃቸው ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ለማዳን ፍቃዱ ሆኖ መረጣት፡፡
- <u>መዝሙር</u>

  ምስራቀ ምስራቃት ሙፅዓ ፀሐይ

  እግዝእትነ ዘመና ሙዳይ

  ዘመና ሙዳይ ማርያም ዘመና ሙዳይ

ይቆየን፡፡